# የንስሐ ሕይወት

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሸኖዳ ፫ኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ

ውርስ — ትርጉም
በዲያቆን እሸቱ ታደሰ ወንድም አገኘሁ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

## ማስታወሻነቱ

የሕይወት ዘመናቸውን ሁሉ ለቅድስት ቤት ክርስቲያን አገልግሎት ሰጥተው በመንፈሳዊ ተጋድሎ ሳሉ ዐረፍተ ዘመን ለገታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሁሉ ይሁንልኝ።

መጀመሪያ በ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ታተመ
ለሁለተኛ ጊዜ በ፲፱፻፺ ዓ.ም. ታተመ
ለሦስተኛ ጊዜ በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ታተመ

የኮምፒዩተር ለቀማና የገጽ ቅንብር፤ ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት
Computer Typesetting and Design by - Ethiopia Book Centre

## ምስጋና

ይህን የትርጉም ሥራ ከመጀመሪያ አንሥቶ ለኅትመት እስከ በቃ ድረስ መንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ ድጋፋቸውንና ማበረታቻቸውን ያለማቋረጥ በመስጠት ከጎኔ ላልተለዩኝ መንፈሳውያን ወገኖቼ:- የለቀማውን ሥራ በጥራት ላከናወኑልኝ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት የኮምፒዩተር ሠራተኞች:- በተለይም ደግሞ የትርጉሙን ረቂቅ ያለመሰልቸት በማንበብ:- በማረምና በማስተካከል እንዲሁም ጠቃሚ ምክራቸውን በመለገስ ለረዱኝ መምህራን ለመልአከ ምሕረት ብርሃኑ ሙሉጌታ እና ለአቶ ግርማ ከበደ የላቀ መንፈሳዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ተርጓሚው

ልጆችን ሁሉ የሚወደን ስለሆነ በኃጢአታችን ብዛት ተስፋ ቆርጠን እንዳንጠፋ ሲል ኃጢአታችንን የሚገልጥልን ቀስ በቀስ ነው። በየጊዜው በሚያጋጥሙን መንፈሳውያን ክስተቶች ውስጥ፤ በምናነባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት፡- በምናያቸው የተለያዩ ነገሮችና ወዘተ.ውስጥ ሊስተካከሉ የሚገባቸውን የተሰወሩ ኃጢአቶቻችንንና መንፈሳዊ ድክመቶቻችንን ይገልጥልናል። እነዚህን ኃጢአቶቻችንንና ድክመቶቻችንን የምናስወግድበት መንፈሳዊ መሣሪያ– ንስሐ እንደሚያስፈልገን እንረዳለን። ከዚህ የተነሣም በክርስትና ሕይወታችን ሁሉ እስከ መጨረሻ አብሮን የሚዘልቀውን የንስሐ ሕይወት እንጀምራለን። ምክንያቱም ዛሬ በአንዱ ኃጢአት የተሸነፈ ሰይጣን ነገ በሌላ ኃጢአት ሊፈትነን ይመጣልና ጦርነቱ አይቋረጥም – በጦርነቱ መውደቅ መነሣት ስላለ ንስሐም ማብቂያ የሌለው የመላሕይወት ባልንጀራ ነው።

ክፉ መሥራት ብቻ ሳይሆን መልካምን ለመሥራት አለመቻልም (አለመሥራት) ንስሐ የሚያስፈልገው ኃጢአት ነው። ሰው ለንስሐ የሚገባ ፍሬ ማፍራት ይጠበቅበታል። በማቴዎስ ወንጌል «እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ» ተብሏልና። ማቴ.፫+፰። ለንስሐ የሚገባ ፍሬን ያደረገ ደግሞ በገላቲያ ፭+፳፪ የተዘረዘሩትን የመንፈስ ፍሬዎች ያፈራል። እንግዲህ መንፈሳዊ ፍሬ ሊያፈራ ሲገባ ፍሬ የሌለው የሆነ ሰው ሊያደርግ የሚገባውን ባለማድረጉ ኃጢአተኛ ስለሆነ ንስሐ መግባት አለበት። ምክንያቱም በመጽሐፍ «በጎ ለማድረግ ዐውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው» ተብሏልና። ያዕ.፬+፲፯።

ስለዚህ ንስሐ አንዴ ፈጽመን የምናልፈውና የምንዘነጋው ሳይሆን በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ከእኛ ጋር የሚኖር ነው። ከሰው ወገን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በስተቀር በምድር ላይ አንድ ቀን እንኳ ቢኖር ከኃጢአት ነጻ የሆነ የለም። ሁላችን ኃጢአተኞች ስለሆንን ለሁላችን ንስሐ ያስፈልገናል። በየዕለቱ ከሥጋዊ ባሕርያችን የተነሣ ከኃጢአት የማንነጻ ከሆነ ንስሐ መግባት ለክርስቲያኖች ሁሉ የዕለት ተግባራችን መሆኑ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን:- እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» በማለት ይህን አረጋግጦልናል። ፩ዮሐ.፩+፰።

## የኃጥአንና የቅዱሳን የንስሐ ሕይወት

ለሰው ሁሉ ንስሐ አስፈላጊ ነው። በየትኛውም ማዕረግና የቅድስና ደረጃ ያሉ ሰዎች ሁሉ ንስሐ ያስፈልጋቸዋል። እንዲህ ሲባል ግን በዓለም የሚኖሩ



የኃጥአን ንስሐና የቅዱሳን ንስሐ አንድ ዓይነት ነው ማለት አይደለም። በኃጥአንና በቅዱሳን ንስሐ መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ።

ኃጢአት የሠሩ በዓለም የሚኖሩ ሰዎች ንስሐ የሚገቡት ፍቅረ እግዚአብሔርን በማጣት ግልጽ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ትእዛዛት በመተላለፍ ስለሚሠሩት ኃጢአት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ቅዱሳን ንስሐ የሚገቡት ወደ ቅድስናና ፍጽምና በሚያደርጉት ጉዞ በሰውነት ባሕርይ የተነሣ ሳላልፈጸሟቸው ጥቃቅን ነገሮች ነው። ልቡናቸው በፍቅረ እግዚአብሔር የተነደፈ ነውና አጉድለናል ወይም አልፈጸምንም ስለሚሉት ነገር ሁሉ ይፀፀታሉ ንስሐም ይገባሉ። ቅዱሳን ንስሐ ይገባሉ ስንል ኃጢአት ሠርተው ነው ማለት እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል።

ቤተ ክርስቲያን በየቀኑ ንስሐ የምንገባበትንና ኃጢአታችንን ስንናዘዝ የምናደርገውን የጸሎት ቅደም ተከተል (ሥርዓት) ሠርታልናለች። በዚሁ መሠረት:-

ሀ. ኃጢአትን ለመምህረ ንስሐ መናዘዝና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን (ቅጣትን) ለመቀበል መዘጋጀት በመዝሙር ፮ እና ፶ ያለውን መጸለይ።

ለ. ስለሠሩት ኃጢአት የእግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ:-

ሐ. እግዚአብሔር በኃጢአቱ ላይ ተፀፅቶ ምሕረት የሚለምነውን ሰው ሁሉ እንዲጠብቅ ስለሌሎች ወገኖችም መጸለይ:-

መ. እግዚአብሔር የይቅርታንና የምሕረትን መንገድ እንዲመራ መለመን:- በመዝሙር ፻፲፰ ያለውን።

ሠ. ስለአለፈው ኃጢአት ራስን መውቀስ፤

ረ. መንፈስን ለንስሐ ማነቃቃት – ሞትን፣ ዳግም ምፅዓትንና የፍርድን ቀን እያሰቡ ይቅርታን መለመን ናቸው።

እነዚህን ስድስት ነጥቦች ዘወትር በጸሎታችን ያስታወስን እንደሆነ በየቀኑና በየሰዓቱ ንስሐን እንድናስብ ያደርጉናል። ስለዚህ ንስሐ መግባት የሚያስፈልግበትን ወቅት አልፈአለሁና ንሰሐ መግባት አያስፈልገኝም የሚባልበት አንዳች ነገርና ምክንያት የለም:- ከፍጹምነት አልተደረሰምና። ከዚህ በመነሣት ነው ንስሐ ለክርስቲያን ሁሉ በዕለት ተዕለት ኑሮው ውስጥ ያስፈልገዋል የሚባለው።

